በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከሜይ 11-20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከሜይ 21-31 እና ከጁን 1-10/2024

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሜይ 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

**እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ** - 1 -

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ - 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት - 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 3 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 4 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 5 -

- 5 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሜይ 21-31, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 7 -

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 7 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከጁን 1-10፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 8 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 8 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 9 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በመካከለኛው፤ በሰሜን ምስራቅ እና ሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ጠንካራ የደመና ሽፋን እና ክምችት የነበራቸው ሲሆን፤ በብዙ ስፍራዎቻቸው ላይም ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል በአለም ተፈሪ 52.2፤ በቡሬ 57.5፤ በዶሎ መና 60.0 እና 30.0፤ በጋምቤላ 46.7፤ በጊዳ አያና 80.0፤ በሊሙ ገነት 43.9፤ በማሻ 30.4፤ በቴፒ 35.2፤ በኮምቦልቻ (ምስራቅ ሀረርጌ) 38.8፤ በባቢሌ 44.0፤ በአድዋ 32.0፤ በአልጌ 40.0 እና 40.6፤ በቡሌ ሆራ 48.0፤ በቦሬ 37.2፤ በጭፍራ 42.5፤ በስንቃጣ 43.9 እና 32.2፤ በአርባ ምንጭ 62.5 እና 43.4፤ በደብረ ማርቆስ 35.8፤ በአቦምሳ 35.0፤ በኢጃጂ 32.1፤ በጋቲራ 64.0 እና 35.8፤ በጅንካ 79.8፤ በላይበር 58.4፤ በማጂ 30.0፤ በቴፒ 35.4፤ በኩርፋ ጨሌ 34.0 በሚ.ሜ ይገኙበታል።

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፤ ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና፣ ምሰራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ አዊ ዞን፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ካማሺ፣ የማኦኮሞ ልዩ ዞን እና መተከል ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ አኙዋክ እና ንዌር፤ ከሱማሌ ክልል ፋፋን እና ሊበን ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ሁሉም የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የምስራቅ፣ ማዕከላዊ እና ሰሜን ምዕራብ ዞኖች፤ ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ ከ31-132 በሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-9 ቀን ያህል ዝናብ ያገኙ ሲሆን፣ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ጀረር፣ ኖጎብ፣ ኤረር፣ አፍዴር እና ዳዋ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አዉሲ፣ ጋቢ እና ሀሪ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ጉጂ፣ ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ፣ ምስራቅ እና ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ከአማራ ክልል ዋህግምራ፣ ሰሜን ወሎ፣ ምዕራብ ጎንደር፤ ከትግራይ ክልል ደቡብ ምስራቅ እና ምዕራብ ዞኖች፣ ከቤንሸንጉል ጉሙዝ ክልል




ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

መተከል ዞን፣ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን ላይ ከ5-30 በሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-4 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲገመገም ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ቡኖ በደሌ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ምስራቅ፣ሰሜን ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ እና አዉሲ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ኤረር፣ ጀራር፣ ኖጎብ፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ሰሜን ምዕራብ እና የምዕራብ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ አኘዋክ፣ ንዌር እና ማዣንግ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ዳዉሮ እና ኮንታ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ ጎፋ እና ጌደኦ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከምባታ እና ጠምባሮ ዞኖች እንዲሁም ሀረር እና ድሬ ዳዋ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡


በሌላ በኩል በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ37-41.2 ዲግሪ ሴልሸየስ ተመዝግቧል (ምስል1) ።





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## ኢ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ቀደም ብለው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ጠቀሜታ ነበረው፡፡ እንዲሁም የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎችን ለመዝራትና ማሳን ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደነበረው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ። በተጨማሪም በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል እንዲሁም የአረንጓዴ እጽዋት ሽፋንን ከመጨመር አንጻር የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡

በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በረባዳማ እና በወንዝ ዳርቻ አካባቢዎች በሚገኙ ማሳዎች ላይ መጠነኛ የሆነ የውሃ በሰብሎች ላይ መተኛት እና በደለል የመሞላት እንዲሁ በጎርፍ የመጠረግ ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ በተጨማሪም በዳውሮና በሌሎች አካባቢዎች ላይ ንፋስና በረዶ የቀላቀለ ዝናብ በሰብሎች፣ በጓሮ አትክልቶችና በቋሚ ተክሎች ላይ ጉዳት እንዳደረሰ የተሰበሰቡ የመስክ መረጃዎች ያመክታሉ(ካርታ 4) ፡፡





ካርታ 4 ኢ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናትበባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌዳዋ፣ በጥቂት የላይኛው ዋቤ ሸበሌ፣ በጥቂት ላይኛው አባይ ተፋሰሶች ከፍተኛ እርጥበት የተስተዋለባቸው ሲሆን በሌላ መልኩ ግን በምዕራብ አጋማሽ በሚገኙ የተፋሰሰ አካባቢዎች ላይ ከመጠነኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ነበራቸው። በአጠቃላይ በሳለፍነው የሜይ አስር ቀናት የተገኘው እርጥበት ለከርሰ ምድር እና ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት መጎልበት አውንታዊ ጎን እንደ ነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥለው የሜይ የመጨረሻዎቹ አሥራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናት ሰፊ ቦታዎችን ያካተተና የተጠናከረ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘም በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተስፋፋ ዝናብ የሚኖር ሲሆን እርጥበታማው የአየር ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6) ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና፤ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም እና አዊ ዞን፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ ካማሺ፣ መተከል እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል  ኮንሶ፣ አማሮ፣ አሌ፣ ቡርጂ፣ ደራሼ፣ ባስኬቶ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ እና ጌዲዮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል  ሀላባ፣ ሃዲያ፣ ጠምባሮ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ አኝዋክ፣ የኢታንግ ልዩ ዞን እና ንዌር ዞኖች፤ ላይ የተሻለ የዝናብ ስርጭት ይኖራቸዋል  (ካርታ 6 )፡፡ በተጨማሪም  ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ) ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ ከአማራ ክልል ዋግህምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች፤የሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ሊበን፤ ዳዋ፣ ሸበሌ እና ኤረር ዞኖች፤ አዲስ አበባ፣ ድሬ ዳዋ እና ሃረር ላይ ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)።



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሜይ 21-31, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ
መጠን በሚ.ሜ


## እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ በጁን በመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ የሀገሪቱን አካባቢዎች ጨምሮ ቀስ በቀስ የሰሜን ምዕራብ ክፍሎችን የሚያዳርስበት ጊዜ ነው ።

በመጪዉ የጁን የመጀመሪያዉ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በምዕራብ አጋማሽ ላይ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 7)



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከጁን 1-10፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት የሚጠበቀው እርጥበት አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎትን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪ ከጁን ጀምሮ  አስቀድመው ለሚዘሩ የመኸር ሰብሎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና ዘር ለመዝራት አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን እንዲሁም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ አካባበዎች የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራትና ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም በአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄ ለተተከሉ የዛፍ ችግኞች እድገት የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066    ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል የሚገኘው እርጥበት በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የእጽዋት ልምላሜን የግጦሽ ሳርንና የመጠጥ የውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች የሚጠበቀው ከፍተኛ እርጥበት በተለይም ረባዳማ በሆኑ ቦታዎች ላይ በሚገኙ የሰብል ማሳዎች ላይ የእርጥበት መብዛት እና ውሃ በሰብሎች ላይ መተኛት እንዳያስከትል የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራት እንዲሁም የጎርፍ መቀልበሻ በማዘጋጀት የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎችን ማከናወን ያስፈልጋል፡

## እ.ኤ.አ  ከሜይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በመካከለኛው እና ታችኛው ተከዜ፣ አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ግቤ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ፣ የስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛወ ዋቤ ሸበሌ እና የገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ተፋሰሶች የተሻለ የውሃ መጠን እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን በተጨማሪም ለመስኖም ሆነ ለሀይል ማመንጫነት የሚያገለግሉ የግድቦችን የውሃ መጠን ያሻሽላል፡፡ ይሁን እንጂ ከባለፉት ወራት ጀምሮ በተለያዩ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ የዕርጥበት መጠን የተስተዋለ ሲሆን፤ በጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አከባቢዎች ላይ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅትና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et